# ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ

## ለቤተሠቦች የሚደረገ ገለፃ

The Royal Women's Hospital የተጨበጠ ነገር ገፅ / www.thewomens.org.au

the women's
the royal women's hospital
victoria australia

***ይህ መረጃ የሚያገለግለው ልጆቻቸው በRoyal Women's Hospital ለሞቱባቸው ቤተሠቦች ጠቃሚ ሲሆን ሆኖም ሁሉም ሐኪም ቤቶች አንድ አይነት አሠራር አይጠቀሙም።***

## ከሞት በኃላ ለምን የህክምና ምርመራ እናደርጋለን

ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ የሚደረገው በተቻለ መጠን ልጅዎ በምን ምክንያት እንደሞተ ለማወቅ ወይንም ለምን አይነት ህመም ህክምና ሲደረግለት እንደነበር ለማወቅ ነው። ምርመራው የሚደረገው በህክምና ጠበብት ፓረንታል ፓቶሎጂስት(perinatal pathologist) በመባል ይታወቃል። ፓረንታል ፓቶሎጂሰት (perinatal pathologist) በዚህ ዓይነት ምርመራ ከፈተኛ ልምድ ያለውና በተለይም ህፃናት ከሞቱ በኃላ በሚደረግ ምርመራ የሰለጠነ ነው። የእርስዎም ልጅ ሁልጊዜ በከፍተኛ ጥንቃቄና ክብር እንክብካቤ ይደረግለታል።

Royal Women's Hospital የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ ከእርስዎ ፍቃድ ውጪ በRoyal Women's Hospital አይደረግም። ምንም አይነት ከሞት በኃላ የህክምና ምርመራ እንዲደረግ ባይፈልጉ እንኳን የእርስዎ ውሣኔ በሐኪም ቤቱ የፍቃደኝነት ማረጋገጫ መሙያ ቅጽ መመዝገብ የኖርበታል።

ከሞት በሁዋላ ወደ ኮረንር መመራት የሚኖርበት ሁኔታም አለ። በእደዚህ አይነት ሁኔታ ከሞት በሁዋላ መደረግ ያለበትን ምርመራ የማዘጋጀት ሃላፊነት የኮሮነሩ ነው። ይህ ሁኔታ የተለመደ አይደለም ምርመራውመ ከመከናወኑ በፊት ሁልጊዜም ከእረስዎ ጋር ውይይት ይደረጋል።

ከሞት በኃላ የሚደረግው የህክምና ምርመራ የሚካሄደው በተቻለ ፍጥነት ወዲያው ህፃኑ እንደሞተ ነው። ይህ ብዙውን ጊዜ የሚደረገው ሕጻኑ በሞተ ከአንድ አስከ ሁለት የሥራ ቀን ውስጥ ነው።

## የተላያዩ አይነቶች ከሞት በኃላ የሚደረጉ የህክምና ምርመራዎች

ከሞት በኃላ ከሚደረግ የህክምና ምርመራ የሚገኘው መረጃ መጠን እንደተመረጠው ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ አይነት ይወስናል።

**ከሞት በኃላ የሚደረጉ የህክምና ምርመራ አይነቶች:-**

***ከሞት በኃላ የሚደረግ ሙሉ የህክምና ምርመራ***

ፓረንታል ፓቶሎጂሰቱ (perinatal pathologist) ለልጅዎ ሙሉ ውጫዊና ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎችን ምርመራ ያካሂዳል። ውስጣዊ የሰውነት ህክምና ክፍል ምርመራ የቀዶ ጥገና ህክምና የሚደረገበት ሲሆን ፓረንታል ፓቶሎጂሰቱ (perinatal pathologist) በጥንቃቄ በሙሉ የውስጥ የሰወነት ክፍልንና ጭንቃላትን በማውጣት ይመረምራል። የወጡትንም የሰውነት ክፍሎቹ ወደነበሩበት ከመመለሳቸው በፊት በሚገባ ይመረመራሉ (እርስዎ አያስፈልግም ከአላሉ በስተቀር)። ከ አካል ህዋሳት ክፍሎች ትንሽ ናሙና ለምርመራ ተወስደው ይቀመጣሉ። ይህ አሰራር በጣም የተሟ‌ሏ ምርመራንና ዝርዝር መረጃን ይሰጣል ሀኖም ይህ ምርመራ የአሟሟቱን ምክንያት በትክክል ለይቶ ለማወቅ ይችላል።

***ከሞት በኃላ የሚደረግ ከፊል ምርመራ***

ፓረንታል ፓቶሎጂሰቱ (perinatal pathologist) ሙሉ ወጫዊ የሰውነት ክፍሉንና አስፈላጊ የሆኑ የተወሰነውን የውስጥ የሰውነት ክፍል ምርመራ ያደርጋል። የትኛው የውስጥ ሰውነት ክፍል እንዲመረመርሎት እንደሚፈልጉ ዶከተሮትን በማማከር እርስዎ ይወስናሉ። በአጉሊ መሳሪያ (ማይከሮስኮፕ) ለመመርመርና ለማስቀመጥ ከሰውነት ህዋሱ ላይ ትንሽ ናሙና ይወሰዳል።

***ከሞት በኃላ የሚደረግ ውጫዊ የሰውነት ክፍል ምርመራ***

ፓረንታል ፓቶሎጂሰቱ (perinatal pathologist) ሙሉ የወጫዊ የሰውነት ክፍሉን ብቻ ምርመራ ያካሂዳል። ውስጣዊ የሰወነትን ክፍል አይመረመርም እንዲሁም ናሙናም አይወሰድም።

*ማንኛውም አይነት ምርመራ ምናልባትም የጨርር ምርመራን(X-ray)፣ ኤም አር አይ(MRI) (ማለትም በማግንቴክ ምስልን በሚየሣይ) (Magnetic Resonance Imaging) እና በፎቶግራፍ መመርመርን ያጠቃልላል።*

***ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራን አለማደርግ***

ልጆዎ ማንኛወንም በበፓረንታል ፓቶሎጂሰቱ (perinatal pathologist) የሚደረግ ምርመራን እንዳይረግለት ሊመርጡ ይችላሉ።

**ከሞተ በኃላ በሚደረግ ምርመራ የሚገኘው የመረጃ መጠን የሚወሰነው ምን ያህል የተሟላ ከሞት በሁዋላ በሚደረግ የህክምና ምርመራ መጠን ነው:ሁሉን ያጠቃለለ የህክምና ምርመራ ከተደረገ በዙ መረጃ ማግኘት ይቻላል።**

## ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ ጥቅሙና ጉዳቱ

***ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ ጥቅሙ***

- ለመሞት ምክንያት የሆኑትን ወይም ለመሞት ምክንያት ያልሆኑትነ መረጃዎች ይሰጠናል
- በማህፀን ወስጥ የህጻኑ እድሜ ምን ያህል አንደነበረ ለማረጋገጥ
- የህጻኑን ጾታ ምን እንደሆነ በመለየት ያረጋግጣል
- በግምት የሞተበትን ሰዓት ያሰወቃል
- የስነ ባህርይው (genetics) ወይም የውጫዊ አካሉ ያስከተለውን ችግርና ያደረገውን ተጽእኖ ይገልፃል
- ለወደፊት በሚረገዝበት ጊዜ ሊያጋጥም ሰለሚችሉ አስጊ ሁኔታዎች መረጃ ይሰጣል
- እናቶችና ልጆችን ለወደፊት ለመርዳት ምርምር በማድረግ መረጃ ይስጣል።

***ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ ጉዳቱ***

- ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ ህፃኑ የሞተበትን ልዩ ምክንያት ሁልጊዜ ላያሰውቅ ይችላል።
- ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ የቀብር ስነሰርዓትን ሊያዘገይ ይችላል ምክንያቱም አጠቃላይ መርመራ ለማከናውን ጊዜ ሰለሚወስድ ነው በተለይም የአካሉ የተላያየ ክፍልን የሰውነት ህዋሱ የሚመረመር ከሆነ። እርስዎ ምርመራው እንዲቀጥል ወይም የቀብር ስነስራቱ እንዲዘገይ ወይንም ህዋሱ/የሰውነት ክፍሉ በሌላ ቀን እንዲቀበር/ እዲቃጠል ሊወስኑ ይችላሉ።

- የውስጣዊ የሰውነት ክፍል ከተደረገለት በኃላ ልጅዎ ጠባሳ ይኖረዋል። ነገር ግን ይህ ጠባሳ ልጁ ልብስ ከለበሰ በኃላ አያስታወቅም።
- ጥቂት ቤተሠቦች ህፃኑ ሙሉ የህክምና ምርመራ ከተደረገለት በኃላ የሚሰማውን የተለየ ስሜት ይገነዘባሉ።

## የሰውነት ህዋሱን ማስቀመጥ

ከሞት በኃላ ለሚደረግ የህክምና ምርመራ የተሰበሰበው ማንኛውም የሰውነት ህዋሱ ቢያንስ ለ23 ዓመት በሐኪም ቤቱ እንዲቀመጥ ህግ ያዛል። ይህም የሚጠቀመው ወደፊት ለልጅዎ ከመጀመሪያው ምን አይነት ምርመራ እንደተደረገለትና ምንም ዓይነት ለወደፊት ጥያቄ ቢነሳ እንደአስፈላጊነቱ ለመመርመር ይረዳል። የተቀመጠው የሰውነት ህዋስ በማህፀን ውስጥ የህጻን መሞትን ለሚመራመሩ ሰዎችም ሊቀርብ ይችላል።

- ምርምሩን አድራጊዎች የሐኪም ቤቱ የስነምግባር ኮሚቴ የሰውነት ህዋሱን ለምርመር እንዲጠቀሙበት ከአለፀደቁ በስተቀር መጠቀም አይቻልም
- ምርመሩ ለእናቶችና ለልጆች ለወደፊት ለሚደረግ ምርመራና ሕክምና ሊረዳ ይችላል።

## የእርስዎ ውሣኔ

ዶክተር ከሞት በኃላ ሰለሚደረግ የህክምና ምርመራና ያነጋግሮታል የሚፈልጉትን ጥያቄ እንዲጠይቁ ወይም ማንኛውንም የሚያሳሰቦትን ነገር እንናገሩ እድል የሰጥዎታል። ውሳኔዎን ከማሳወቅዎ በፊትና የስምምነቱን ቅፅ ከመሙላትዎ በፊት የጠየቋቸው ጥያቄዎችዎ እንዲመለስልዎት ማድረጉ ጠቃሚ ነው።

ምንም አይነት ትክክልኛ ወይም የተሣሣተ የሚባል ምርጫ የለም ምናልባትም የእርስዎ የመጨረሻ ውሳኔ የሚወሰነው እንደ ሟች ልጅዎ እድሜ መጠን ወይንም የልጅዎ አሟሟት ሁኔታ ይሆናል። እንዲሁም በእርስዎ ባህልና እምነት ላይ ተመርኩዞው የሰጡት ውሳኔ ሊሆን ይችላል።

## ከሞት በኃላ ከሚደረግ የህክምና ምርመራ በኃላ

ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ ብዙን ጊዜ የሚጠናቀቀው ህፃኑ ከሞተ ከአንድ ወይም ሁለተ የስራ ቀናቶች ውስጥ ነው። የምርመራው ስርአት ከተከናወነ በሁዋላም በሐኪም ቤት ውይም የቀብር ስነስራት በሚዘጋጅበት ስፍራ ልጅዎን ማየትም ወይም ማቀፍ ይችላሉ።

በፔሪናታል ፓቶሎጂስቱ (perinatal pathologist) ከምርመራ ያገኘውን ዝርዝር ዘገባ ያቀርባል። ይህም ብዙዉን ጊዜ ከ 8 እስከ 12 ሣምንት ውስጥ ይጠናቀቃል። ልጅዎ በ (Royal Women's Hospital) ከተወለደ ወይም አዲስ በተወለዱ ህፃናት እንክብካቤ ማድረጊያ እንክብካቤ የተደረገለት ከሆነና የተለየ እንክብካቤ በሚደረግበት አከባቢ ከአለ ብዙ ልምድ ከአላቸው ዶክቶሮች (ከአዋላጅ ዶክተር ወይም በማህጸን ውስጥ ያሉን ልጆች ከሚያክም ሀኪም) ሰለተገኘው ምርመራ ለመወያየት ከፈለጉ ቀጠሮ ሊሠጥዎት ይችላል። ሌላው አማራጭም ሪፖርቱ ለግል አዋላጅ ሐኪምዎ ወይም መደበኛ ሐኪምዎ እንዲላክሎት መጠየቅ ይችላሉ።

## ማጠቃሊያ

- ከሞት በኃላ በሚደረግ የህክምና ምርመራ ልጅዎ በምን ምክንያት ሊሞት እንቻለ መረጃ ይሰጣል።
- ከሞት በኃላ የሚደረግ ህክምና ምርመራ ከእርስዎ ፍቃድ ውጪ አይደረግም።
- ከሞት በኃላ የሚደረግ ህክምና ምርመራ እንዲደረግ የሰጡበት የእርስዎ ወስኔ በሐኪም ቤቱ የፍቃደኝነት መስጫ ቅፅ የግድ መመዝገብ ይኖርበታል።
- ህፃኑ ከሞተ በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራን ዝርዝር እርስዎ ሊወስኑ ይችላሉ።
- ከሞት በኃላ የሚደረግ ህክምና ምርመራ ውጤት ለማግኘት ከ8 እስከ 12 ሣምንታት ይወስዳል።
- ማንኛውም ከሰውነት ህዋሱ የተወሰደ ናሙና ቢያንስ ለ23 አመት ይቀመጣል።

**ለበለጠ መረጃ**

በዚህ መግለጫ ውስጥ ሰለተገለጹት ነገሮች ለመወያየት ከፈለጉ የውመን Women's ሀኪም ቤትን በ (03) 8345 2000 (የስልክ መስመሮችን ማገናኛ ክፍል) በመደወል የእርስዎን አበራታች ሰረታኛ ወይንም እርስዎ እንክብካቤ ያገኜበትን ክፍል/አከባቢ እንዲያገናኝዎት ይጠይቁ። ከሞት በኃላ የሚደረግ የህክምና ምርመራ ወይም በአደጋ ለሚደርስ ሞት ምርመራ መረጃ ለማግኘት በ 1300 309 519 መደወል ይችላሉ።

**ሴቶች ሆሲፒታል ውስጥ ከሲጋራ ማጭስ ነጻ ነው። ለበለጠ መረጃ እና ድጋፍ ላማግኝት www.quit.org.au ይጎብኙ።**

ማሳሰቢያ የሮያል ሴቶች ሆስፒታል(The Royal's Hospital) በዚህ የመረጃ መግለጫ ለተሰጠው መረጃም ሆነ ምክር ለማንም ሰው ሃላፊነቱን አይወስድም። ይህን መረጃ ያቀረብነው ማንም መረጃው የሚጠቀመው ከሆነ የመረጃውን አግባብነትና ትክክለኛነት በማመዘን ይጠቀሙበታል በሚል ግምት ነው። ሴቶች ሰለጤንነታቸው ከጤና ባለሙያ ጋር መወያየት ይኖርባቸዋል። ሰለጤንነትዎ የሚያሳስብዎ ነገር ካል ከጤና አገልለግሎት ሰጭዎ ምክር መጠየቅ ይኖርቦታል; ወይም አሰቸኳይ የጤና እንክብካቤ ካሰፈለግዎት ወደ አቅራቢያዎ የሚገኝ ሆሰፒታል ድንገተኛ ክፍል መሄድ ይኖርቦታል። © የሮያል ሴቶች ሆሰፒታል(The Royal's Hospital)፣ ሜይ May 2008